# የብሔር (ጎሣ) ግጭት መንስዔዎችና መፍትሔዎቹ

ኢትዮጵያ የበርካታ ብሔርና ብሔረሰቦች ሀገር ናት። በሀገሪቱ ከ81 ያላነሱ የተለያዩ ቋንቋ፣ ባህል፣ ኃይማኖትና የኑሮ መሠረት (Livelihood) ያላቸው ብሔረሰቦች አሉ። ይህን በአንክሮ የተመለከቱት ጣሊያናዊው ታሪክ ተመራማሪና ፀሐፊ ፕ/ር ኤንሪኮ ቼሩሊ በአንድ ወቅት በጻፉት ጽሑፍ "ኢትዮጵያ የሕዝቦች ሙዝየም ናት /Ethiopie Museo di popoli/ ሲሉ አሥፍረዋል። በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ብሔርና ብሔረሰቦች ለረጅም ዘመናት የቆየና የዳበረ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ትስስር እንደነበራቸውና አሁንም እንዳላቸው ግልጽ ነው። ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ ከረጅም ዘመናት ጀምሮ፣ በተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች መካከል በተለያዩ ምክንያቶች ግጭቶች ነበሩ። እነዚህ ግጭቶች ከዘመን ዘመን መንስዔያቸውንና መልካቸውን እየቀያየሩ አሁን ካለንበት ጊዜና ደረጃ ላይ ደርሰዋል። የዛሬው የእንቢልታ "አጀንዳ" የብሔር ግጭት አሁን ያለበትን ደረጃ መንስዔዎቹንና መፍትሔዎቹን በዘርፉ ጥናትና ምርምር ያካኼዱ ምሁራንን ሃሳብና ጽሑፎች በማካተት ይተነትናል።

## ብሔር (ብሔረሰብ) ጎሣ እና ግጭት

ብሔር እና ጎሣ የሚሉት ቃላትና ስያሜዎች፣ ለረጅም ጊዜ የሥነ-ባህል እና የቋንቋ ምሁራን ሲያወዛግቡ የኖሩ ናቸው። የጋራ ቋንቋ፣ ባህል፣ ታሪክ፣ የመሬት ይዞታ እና መነሻ የዘር ሀረግ (Commen ancestry) ያለውን ሕዝብ፣ አንዳንድ ሊቃውንት "ብሔር" ብለው ሲጠሩት ሌሎቹ ደግሞ ጎሣ ይሉታል። የተወሰነ ልዩነት ቢኖርም ከቅርብ ዘመናት ጀምሮ በምሁራንና በሌሎች ሰዎችም ዘንድ "ብሔር" የሚል መጠሪያ ስያሜ የሚሰጠው ሕዝብ የጋራና ከሌላው የተለየ ቋንቋ፣ ቁሣዊና መንፈሣዊ ባህል (አንዳንዴ ኃይማኖትንም ሊጨምር ይችላል) ሁሉም የሕዝቡ (ማኅበረሰቡ) አባል የኔነው የሚለውና ያለፈበት ታሪክ እና ለረጅም ዘመናት የኖረበት የመሬት ይዞታ ያለውን ሕዝብ ነው።

እነዚህ አራት ነገሮች በአንድ ላይ ሲጣመሩ፣ ሕዝቡ የጋራ ሥነ ልቦና እና ከሌላ ሕዝብ የተለየ የአንድነትና የአብሮነት ስሜትና አስተሳሰብ በመፍጠር፣ ማንነቱንና ምንነቱን (Identity) አጉልተው ያወጡታል። ጎሣ በሚል ስያሜ የሚጠራ ሕዝብ ደግሞ አንድን (ኅብረተሰብ) ብሔር የሚያሰኙትን አራት ነጥቦች ያካተተ ሆኖ የሕዝቡ የጋራ የሆነ መነሻ የዘር ሐረግን (Common ancestry/origin) ይጨምራል። በመሆኑም አንድን ሕዝብ ጎሣ ተብሎ እንዲጠራና እንዲፈረጅ የሚያደርገው የጋራና አንድ የሆነው የዘር ሐረግ ምንጩ፣ እንጅ የጋራ ቋንቋ፣ ባህል፣ ታሪክና የመሬት ይዞታ አይደለም።

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ- መንግሥት ጎሣ የሚለውን ጽንሰ ሃሣብ (Concept) እና ስያሜ አያካትትም፣ አይዳስስምም። ነገር ግን "ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝቦች በሚል ለሚያካትተው ጽንሰ ሃሣብና ስያሜ ያስቀመጠው ትርጉም ግን፣ አስቀድሞ ለብሔር ከተሰጠው ትርጉም ጋር በእጅጉ የሚመሳሰል ነው። የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 39 ቁጥር 5 ... በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ "ብሔር፣ ብሔረሰብ፤ ሕዝብ ማለት ... ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንጸባርቅ ባሕል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፤ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑ፣ የሥነ ልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያያዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ ናቸው" ይላል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ሕዝቦች፣ በየራሳቸው ብሔር ናቸው ብሎ መፈረጅ አስቸጋሪ ነው። አንዳንዶቹ ሕገ መንግሥቱ ያስቀመጠውንና ምሁራን የሚስማሙበትን የብሔር (ብሔረሰብ) መሥፈርት ያሟላሉ። ለዚህ ምሣሌ የሚሆኑት የአፋር፣ ትግሬ፣ አማራ፣ ሶማሌ እና ሌሎችም ብሔሮች ናቸው። አንዳንድ ሕዝቦች ደግሞ የብሔር መስፈርትን የማያሟሉና ጎሣም፣ ብሔርም ብሎ ለመፈረጅ የሚያስቸግሩ ናቸው። ይህም የሚሆነው ተወራራሽ ቋንቋ፣ ባህል ወይም የሥነ ልቦና አመለካከት (ጠባይ) ከሌላው ሕዝብ ጋር ስለሚጋሩና የመሬት ይዞታቸውና አሰፋፈራቸውም ከሌሎች ሕዝቦች የተሠባጠረ ስለሆነ ነው።

የብሔር (የጎሣ) ግጭት የሚባለው፣ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የብሔር (ጎሣ) አባላት መካከል በተለያየ ምክንያት የሚነሳ ግጭትና፣ ግለሰቦች በተናጠልም ሆነ በጋራ ብሔራቸውን (ጎሣቸውን) መሠረት ያደረገ ልዩነት ተንተርሰው፣ የሌላውን ብሔር ጎሣ አባል የሚያጠቁበት ትራጀዲያዊ ድርጊት ነው። የብሔር የጎሣ ግጭት በኢትዮጵያ የረጅም ዘመን ታሪክ እንዳለው በመስኩ ጥናትና ምርምር ያደረጉ ምሁራን ይናገራሉ። በጉዳዩ ዙሪያም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተለያየ ይዘት ያላቸው ጥናቶች ተደርገዋል። የብሔር (ጎሣ) ግጭቶች የረጅም ጊዜ ታሪክ ቢኖራቸውም በተደጋጋሚና በስፋት የሚከሠቱት ግን በተወሰኑ አካባቢዎች ነው። የአፋርና ሶማሌ፣ የአፋርና አማራ፣ የኦሮሚያ (ቦረና) እና የደቡብ ሕዝቦች አዋሣኝ ቦታዎች በተጨማሪም የጋምቤላ፣ ኦሮሚያ እና ቤንሻንጉል ክልሎች፣ የብሔር ግጭት በተደጋጋሚ ከሚከሰትባቸው አካባቢዎችና ክልሎች ዋናዎቹ ናቸው። በአፋርና በኢሣ ሶማሌዎች፣ በቦረና ኦሮሞዎችና በሶማሌ፣ በአርቦሬ እና በጉጂ ኦሮሞዎች እንዲሁም በአፋርና በጂሌ ኦሮሞዎች፣ በአርጐባዎች መካከል የሚደረጉ ግጭቶች ለዘመናት የቆዩ ናቸው።

የብሔር ግጭቶች አዳዲስ መልክና ገጽታ ይዘው የቀጠሉ ሲሆን፣ በመንግሥት መዋቅራዊና አስተዳደራዊ ለውጥ የተከሰቱ አዳዲስ የ1983 ዓ.ም. የመንግሥት ለውጥን ተከትሎ፣ ነባር ግጭቶችም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተስተውለዋል። ለመጥቀስ ያህልም በ1984 ዓ.ም. በአርባ ጉጉ እና በደኖ፣ በ1983 እና 84 ዓ.ም. ጀምሮ በቦረና ዞን ከ1984 ዓ.ም. ጀምሮ በጉጂ አካባቢ፣

በ1996 ዓ.ም. በጋምቤላ እና በቅርቡ ደግሞ በምዕራብ ወለጋ ዞን፣ ደም ያፋሰሱና በርካቶችን ለሕልፈተ ሕይወትና ከቀያቸው ለመፈናቀል የዳረጉ የብሔር ግጭቶች ተካኼደዋል።

## <u>መንስዔዎች</u>

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በረዳት ፕሮፌሰርነት የፌደራሊዝምና የሕግ ተቋም ዳይሬክተር የሆኑት ዶ/ር አሰፋ ፍስሐ በኢትዮጵያ የጎሣ ግጭት የሚባል የለም ባይ ናቸው። የጎሣ ግጭት የሚባለው "እከሌ" የተባለው ጎሣ እከሌ ከተባለው ጎሣ ጋር ተነስቶ መጋጨት ማለት ነው። በኢትዮጵያ ያለውን የአብዛኞቹ ግጭቶች መነሻ ሲታዩ ፍትሐዊ የሆነ የሥልጣን ክፍፍል አለመኖርና ሪሶርስ (ሀብት) ፍትሐዊ በሆነ መንገድ አለመከፋፈል፣ ከማንነት (identiey) ጥያቄ ጋር ተዳምረው ዋነኛ የግጭት መነሻ እንደሆኑ ይጠቁማሉ።

በዶ/ር አሰፋ አስተያየት፣ በኢትዮጵያ እየታዩ ያሉት ግጭቶችና መንስዔዎቻቸው ፍትሐዊ የሥልጣንና የሪሶርስ (Resource) ክፍፍል አለመኖር እስከሆነ የማንነት ጥያቄው መንስዔ ሳይሆን፣ የግጭት አባባሽ በመሆኑ የጎሣ ግጭት አለ ብሎ ደፍሮ ለመናገር ያስቸግራል ይላሉ።

በአፍሪካ ቀንድ ፖለቲካ ለረጅም ጊዜ ጥናትና ምርምር ያካኼዱት ፕ/ር ጆን ማርካኪስ "የጎሣ ግጭትና መንግሥት በአፍሪካ ቀንድ" (Ethnic Conflict and the State in the Horn of Africa) በሚል ርዕስ ባዘጋጁት ጥናታዊ ጽሑፍ ሀብትን (Resource) ለመያዝ የሚደረግ ፉክክር፣ መንግሥት ሀብትን (Resource) በማከፋፈል ረገድ የሚጫወተው ሚና እና የመንግሥት አስተዳደራዊ መዋቅር፣ በኢትዮጵያ ለሚታዩት የብሔር ግጭቶች ዋነኛ መንስዔ ናቸው ይላሉ።

አንድ ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ የታሪክ ምሁርና ተመራማሪ እንደገለጹት፣ የሀገራችን የብሔር ግጭቶች ዋነኛ መንስዔ፣ የ1983 ዓ.ም. የመንግሥት ለውጥን ተከትሎ የተዘረጋው አዲስ የፖለቲካ መዋቅር ነው ይላሉ። በብሔር ላይ የተመሠረተው ይህ ፌደራላዊ መዋቅር፣ የተለያዩ ብሔረሰቦችና ጎሣዎች ለመሬት ይዞታና ለሪሶርስ ባለቤትነት ትኩረት እንዲሠጡ ስላስገደዳቸው፣ የብሔር (ጎሣ) ግጭቶች ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ሁኔታ እንዲስፋፉና እንዲባባሱ ዋና ምክንያት ሆኗል። እኚሁ ምሁር እንደሚሉት ሁሉም እንኳ ባይሆኑ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፣ በሀገራችን የተለያዩ ክፍሎች እየታዩ ያሉት የብሔር (የጎሣ) ግጭቶች መንስዔ፣ ተቃራኒና ተቻቻይ ያልሆኑ የኑሮ መሠረቶች (Conflicting and Contrasting livelihoods)፣ በየክልሎች /በየወረዳዎች/ ባሉ የአስተዳደር ቦታዎችና መዋቅሮች ፍትሐዊ ያልሆነ የሥልጣን

ክፍፍልና ውክልና አለመኖር፣ አንድ ብሔር የመረጃና የዞን አስተዳደራዊ መዋቅር ቦታዎችን በብዛትና በበላይነት የመያዝ ፍላጐት ናቸው።

ረ/ፕሮፌሠር መድኃኔ ታደሰ የጋምቤላን ግጭት መሠረት አድርገው ባደረጉት ጥናት እንዳረጋገጡት፤ የጋምቤላ ግጭት መንስዔ የኑዌር ጎሣዎች የኑሮ መሠረት የሆነው አርብቶ አደርነት (Postoralism) የአኝዋክ ጎሣዎች የኑሮ መሠረት የሆነውን የእርሻ (ግብርና) መቃረኑና ከጊዜ ወደ ጊዜም የአኝዋክ የእርሻ ቦታዎች፣ በኑዌር አርብቶ አደሮች መያዛቸው ነው። ከዚህ በበለጠ ሁኔታ ደግሞ የኑዌር ጐሣዎች በክልሉ እና በውስጡ የሚገኙ የዞንና ወረዳ አስተዳደር መዋቅሮች የበላይነት መያዛቸው፣ ሁለቱን ወገኖች ወደ ደም አፋሳሽ ግጭት እንዲያመሩ አስገድዷቸዋል።

ዶ/ር አሰፋ በሕገ መንግሥቱ መሠረት ሥልጣን ከማዕከላዊው መንግሥት ወደ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች፣ በየደረጃው እንዲወርድ መደረጉ የብሔር ግጭቶች በአዲስ መልክ እንዲቀሰቀሱ አላደረገም ባይ ናቸው፤ ነገር ግን በየደረጃው የሚገኙ የፖለቲካ ኃይሎች እነዚህን በሕገመንግሥቱ ላይ የተቀመጡትን መመሪያዎች ለመፈፀም ባለመቻላቸው ወይም የራሳቸውን ችግር በማስቀደማቸው የሚፈጠሩ ግጭቶች እንደሆኑ ይገልፃሉ። ሥልጣንን ወደ ክልሎችና ወረዳዎች ማውረዱ፣ ለብሔር ብሔረሰቦችም ሥልጣን የሚጋሩበትና የሚወከሉበት መድረክና መንገድ (Power Sharing Scheme) መፍጠሩ ስህተት ሆኖ ሳይሆን፣ በአንዳንድ ክልሎች በርካታ ብሔረሰቦች (ጎሣዎች) ከመኖራቸው አንፃር፣ የክልሎቹ አስተዳደራዊ መዋቅር በክልሉ ውስጥ ያሉትን ብሔሮች ሙሉ በሙሉ በሚያቅፍ ሁኔታና ሁሉም በሚቀበሉት መልኩ አለመዋቀሩ ነው።

"የሪሶርስ (ሀብት) ክፍፍሉ ኢ-ፍትሐዊነትም በክልሎችና በወረዳዎች ከሰፈነው የመልካም አስተዳደር ችግር ጋር ስለሚያያዝ ፖለቲካዊ ገጽታው ያመዝናል" የሚሉት ደግሞ ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉት የታሪክ ምሁር ናቸው። እንደ እርሳቸው አመለካከት እና የጥናት ተሞክሮ ከሆነ፣ እንደ ጋምቤላ፣ ደቡብ ሕዝቦች (ጎሣዎች) ክልሎች በአስተዳደር መዋቅሩ በብዛት ውክልና እና የበላይነት ያገኘ (ያለው) ብሔር (ጎሣ) በክልሉ የሚገኝ መሬትና ሀብትን እንዲሁም ለክልሉ ከማዕከላዊው መንግሥት የሚመደብለትን የፋይናንስ በጀት የራሱን ብሔር አባላት በሚጠቅም መልኩ ኢፍትሐዊ ክፍፍል ያደርጋል። ስለዚህም የሪሶርስ (ሀብት) ክፍፍልን በበላይነት በማሽከርከር፣ የግጭት መንስዔ የሚያደርገው በየክልሎችና ወረዳዎች የሰፈነው አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ችግር ነው።

በኢትዮጵያ ላለው የብሔር (ጎሣ) ግጭት በርካታ መንስዔዎች ያሉት ቢሆንም፣ ጥናቶች የሚያመለክቱትና የመስኩ ምሁራን እንደሚናገሩት ከሆነ ከ1983 ዓ.ም. ወዲህ የተከሰቱት

ግጭቶች ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ መንስዔ፣ የሽግግር መንግሥቱ ቻርተር እና በኋላም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት ተግባር ላይ ያዋለው፣ ብሔርን መሠረት ያደረገ የፌደራል የመንግሥትና የአስተዳደር አወቃቀር ሥርዓት ነው።

## የሕገ መንግሥቱና የፌደራል ሥርዓቱ አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖዎች

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት መሠረት፣ የኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት በዘጠኝ ክልሎች የተዋቀረ ነው። የፌደራል መንግሥቱን ክልሎች አወቃቀር አስመልክቶ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 46 ቁጥር 2 ክልሎች የሚዋቀሩት በሕዝብ አሰፋፈር፣ ቋንቋ፣ ማንነትና ፈቃድ ላይ በመመሥረት ነው ይላል። ይህን መሠረት በማድረግ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 47 ላይ እንደሠፈረው፣ አዲስ አበባንና ድሬዳዋን ሳይጨምር ሀገሪቱ በዘጠኝ ክልሎች ተዋቅራለች ማለት ነው።

ስለዚህም በሀገራችን ሕገ መንግሥቱ ያስቀመጠውን የብሔር ብሔረሰብና ሕዝቦች የመባል መሥፈርት የሚያሟሉ ከዘጠኝ በላይ ብሔረሰቦች እንዳሉ ግልጽ ነው። ከዚህም በመነሳት አብዛኞዎቹ በብሔር (ጎሣ) ግጭት ዙሪያ ጥናት ያደረጉ ምሁራን "ሕገ መንግሥቱ ለብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ በክልል ደረጃ የመዋቀርን መብት ከሰጠ በኋላ በምን መሥፈርትና ፍልስፍና ዘጠኝ ክልሎች ብቻ እንደተመረጡ ግልጽ አይደለም" የሚል ሂስ ይሰነዝራሉ። ከዘጠኙ ክልሎች ስድስቱ (ትግራይ፣ አፋር፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሶማሌ እና ሐረሪ) ብሔራዊ (አንድ ብሔር ብቻ የሚያካትቱ) ክልሎች ናቸው፡ ቀሪዎቹ ሦስት ክልሎች ጋምቤላ፣ ደቡብ እና ቤንሻንጉል ከአንድ በላይ ብሔሮችን ያካተቱ ሕብረ ብሔር ክልሎች ናቸው።

ዶ/ር አሰፋ እንደሚሉትም የሕገ መንግሥቱና የፌደራል አወቃቀሩ፣ የአዲስ ሥርዓትና ሀገር ግንባታ ሂደቱ (nation building) በአውሮፓ እና በአሜሪካ ካለው ጋር ተዛማጅነት ያለው ሆኖ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮችን መነሻ እንዳደረገ ያብራራሉ። በመጀመሪያ በቀደሙት ሥርዓቶች ሥልጣን በማዕከላዊው መንግሥት ብቻ የተያዘና በተለያዩ አካባቢዎች ያሉ ብሔርና ብሔረሰቦች የሥልጣን ባለቤት ስላልነበሩ፣ ሕገ መንግሥቱና የፌደራል አወቃቀሩ ሥልጣንን ወደ ታች በማውረድ ብሔር ብሔረሰቦች በፌደራል መዋቅሩ መሠረት ተጋሪ የሚሆኑበትን መንገድ መፍጠር ነው።

ሁለተኛው፡- በቀደሙት ሥርዓቶች፣ የብሔር ብሔረሰቦች የማንነት ጥያቄ ቦታ ያልተሰጠው በመሆኑ ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ በራስ ቋንቋ ባህል እና መሬት እራስን የማስተዳደርን ጉዳይ ለማስተናገድ ነው። ይሁን እንጂ የክልሎች አወሳሰን በግልጽ መርኅና

ፍልስፍና ላይ የተመሠረተ አለመሆኑን በመጥቀስ በርካቶች ቅሬታ እንደሚያሰሙ ይገልፃሉ። ለዚህ እንደምሣሌ የሚጠቅሱት የሐረሪ ብሔርን በክልል ደረጃ መዋቀር ነው። በደቡብ ክልል ከሐረሪ ብሔረሰብ በሕዝብ ብዛትም ሆነ በያዙት መሬት የቆዳ ስፋት የላቁ ሕዝቦች እያሉ፣ በክልል ደረጃ አለመዋቀራቸው ጥያቄ ያስነሳል። ሥልጣንን ወደ ሕዝብ፣ ብሔርና ብሔረሠቦች ማውረዱና የመብትና የሥልጣን ባለቤት ለማድረግ በሩን መክፈቱ፣ ብሎም ደግሞ ለረጅም ዘመናት ትኩረት ያልተሰጠውን የማንነት ጉዳይ ለማስተናገድ ምቹ ሁኔታ መፍጠሩን፣ የሕገ መንግሥቱና የፌደራል ሥርዓቱ ዋነኛ አሉታዊ ገጽታ መሆኑን ዶ/ር አሰፋ ያሠምሩበታል።

ረ/ፕሮፌሠር መድኃኔ ታደሰ በኢትዮጵያ ጠረፎች ግጭቶችን የመፍታት ጥረት (The Quest for Conflict Settlement in Ethiopia's Periphery) በሚል ርዕስ በ2006 (እ.ኤ.አ.) ባሣተሙት መጽሐፍ፣ ከ1983 ዓ.ም. በኋላ የተመሠረተው የፌደራል አወቃቀር፣ ከአወንታዊ አስተዋጽኦው አሉታዊ ተጽእኖው እንደሚያመዝን ይጠቁማሉ። ከ1983 ዓ.ም. በፊት በነበረው አስተዳደራዊ መዋቅር፣ የተለያዩ ብሔሮችና ጎሣዎች ድንበርን ያለብዙ ማመንታትና ማቅማማት ይቀበሉ ነበር። ይህም የሆነበት ምክንያት እንደ ግጦሽ መሬት ውሃ እና የመሳሰሉት ሀብቶች፣ በየትኛውም የአስተዳደር ክልል ቢካተቱ፣ የማንኛውም ብሔር የመጠቀም መብት የተጠበቀ ስለነበረ እና ማንኛውም ብሔር የመጠቀም እንጂ የባለቤትነትና የአጠቃቀም ወሣኝነት መብት ስላልነበረው ነው። ከዚህ በተቃራኒ ከ1983 ዓ.ም. በተለይም የሕገ መንግሥቱን መርቀቅና መተግበር ተከትሎ የመጣው የፌደራል ሥርዓትና አከላለል፣ አንድን ብሔር በክልሉ ባሉ ሀብቶች (Resources) የባለቤትነት እና የአጠቃቀም ወሣኝነት መብት ስለሠጠው እያንዳንዱ ጐሣና ብሔር ለድንበር ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት እንዲሠጥ አስገድዶታል። ረ/ፕሮፌሠር መድኃኔም ሆኑ ዶ/ር አሰፋ እዚህ ላይ እንደ ምሣሌ የሚጠቅሱት፣ በአፋርና በኢሣ መካከል ያለውን ግጭት ነው። በሁለቱ መካከል የነበረው ግጭት፣ በቅድመ 1983 ዓ.ም. የፍትሐዊ የግጦሽ መሬትና የውሃ አጠቃቀም ነበር። ከድህረ 1983 ዓ.ም. በኋላ ግን ወደ ባለቤትነት ጥያቄ ተሸጋግሮ ከጐሣዎች ግጭት ወደ ክልሎች ግጭት ተሸጋግሯል።

የኢትዮጵያ የፌደራል ሥርዓትና የክልሎች አወቃቀር እንደ ሌላው የአፍሪካ ቀንድ ሀገሮች ሁሉ፣ ብሔርን (ጎሣን) ማዕከል ያደረገ (Ethnocentric) ሆኗል ሲሉ ፕ/ር ማርካኪስ አስቀድሞ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው ይገልፃሉ። ፕ/ር ማርካኪስ የክልሎች አወቃቀር ብቻ ሳይሆን የፌደራል መንግሥቱ ዋና መሠረትም የብሔር (የጐሣ) ማንነትን ማዕከል ያደረገ በመሆኑ፣ የኢትዮጵያን መንግሥትና ሀገር ኢትኖሴንትሪክ ስቴት (Ethnocentric State) ብለው ይፈርጁታል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የብሔር (የጎሣ) የማንነት ጥያቄ፣ ሙሉ በሙሉ ፖለቲካዊ ገጽታ እየያዘ በመምጣቱ፣ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ማኅበረሰብና ሕዝብ መካከልም የቋንቋ፣

የባህል፣ የታሪክ እና የመሬት ይዞታ ልዩነቶችን ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ልዩነቶችን እያሠረፀ መጥቷል።

"በአንዳንድ አካባቢዎች ከተሞችንም ጨምሮ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ግንኙነቶች ብሔርን (ጎሣን) መሠረትና ማዕከል እያደረጉ በሕገ መንግሥቱ የተመለከተው የብሔር መብትና እኩልነት አቅጣጫውን ስቶ ወዳልተፈለገ መንገድ እየገባ ነው።" ይላሉ ፒ/ር ማርካኪስ። አያይዘውም "ብሔር (ጎሣ) በኢትዮጵያ የፖለቲካ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ኀልውና ዋና ተዋናይ ሆኗል። የአንድን ብሔር (ጎሣ) አባላት ወደጋራ ውሣኔና ድርጊት የሚያነሳሳቸው ምክንያትም ያለፈው ጊዜ ታሪካቸውና ማንነታቸው ሳይሆን አሁን ወይም ወደፊት ይመጣል ብለው በታሳቢ የሚያስቀምጡት ሥጋትና ምኞት ነው።" ባይ ናቸው።

ስማቸው እንዲጠቀስ ያለፈለጉት የታሪክ ምሁሩ ደግሞ፣ ሕገ መንግሥቱንና የፌደራል ሥርዓቱን፣ ከሁለት ተቃራኒ አቅጣጫ የሚመለከቱ ሁለት ወገኖች እንዳሉ ይገልፃሉ። በአንደኛው ወገን ያሉት ሕገ መንግሥቱና የፌደራል ሥርዓቱ ሀገሪቱን ከመበታተን በስተቀር የመገንባትና የብሔር እኩልነትና መብት የማስፈንና የማስከበር አስተዋጽዖ የለውም የሚሉት ሲሆኑ፣ በሌላኛው እና በተቃራኒው ጫፍ ያሉት ወገኖች ደግሞ፣ ሕገ መንግሥቱና የፌደራል ሥርዓቱ፣ የብሔር እኩልነትን በማስፈንና ማንነታቸውን አስከብሮ፣ ሀገሪቱ ፍጹም አንድነት የሰፈነባትና ዘላቂ ህልውና ያላት በማድረግ ረገድ ያበረከተው ሚና የተዋጣለት ነው የሚሉት ናቸው።

ምሁሩ "ሁለቱም ወገኖች የተሳሳቱ ናቸው የሚል አቋምና አመለካከት አላቸው። ለዚህ ዓይነተኛ ማስረጃ ነው ብለው የሚጠቅሱት፣ ከሕገ መንግሥቱ ሥራ ላይ መዋል እና ከፌደራል ሥርዓቱ መዘርጋት በኋላ፣ ቀድሞ የነበሩ ግጭቶች መጥፋታቸው ወይም መቀነሳቸው፣ በአንፃሩ ደግሞ የሕገ መንግሥቱን መርኅና የፌደራል ሥርዓቱን አወቃቀር መነሻ ያደረጉ ግጭቶች መከሰታቸው ነው። በቀድሞዎቹ መንግሥታት በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች በተለይም በጠረፋማ አካባቢዎች የነበሩ ብሔረሰቦች፣ አንደኛውን ብሔር የመንግሥት እና የሥልጣን ባለቤት አድርጎ ራሣቸው ደግሞ ባይተዋር አድርገው በመቁጠር ያደርጉት የነበረ ግጭት በአብዛኛው አካባቢ ጠፍቷል ወይም መጠኑና ድግግሞሹ ቀንሷል። ይህ ሕገ መንግሥቱና ፌደራላዊ ሥርዓቱ ያመጡት ለውጥ ነው። በሌላ በኩል ግን የፌደራል ሥርዓቱ አወቃቀርና የክልሎች የውስጥ አስተዳደራዊ መዋቅር፣ ብዙ ግጭቶችን ፈጥረዋል። በመሆኑም የፌደራል ሥርዓቱ እና ሕገ መንግሥቱ ያስቀመጧቸው መርሆች ትክክል ሆነው ሳለ ችግሩ የሚመነጨው፣ ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የማጣጣምና በትክክል የመተግበር ጥረት፣ በተገቢው መንገድና ፍጥነት አለመከናወኑ ላይ ነው።

## ከብሔር ክልላቸው ውጭ የሚኖሩ ዜጎች ችግር

በኢትዮጵያ የሚገኙ የተለያዩ ብሔረሰብ (ጎሣ) አባላት፣ ለረጅም ዘመናት ብሔራቸው ከሚኖርበት ቦታ ወይም ክልል ውጭ ሲንቀሳቀሱና ሲሰፍሩ ኖረዋል። በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 32 መሠረት፣ ማንኛውም የሀገሪቱ ዜጋ፣ በሕጋዊ መንገድ በማናቸውም የሀገሪቱ ክፍል የመዘዋወር፣ የመኖርና የመሥራት መብት አለው። ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ በመጣው አዲስ የመንግሥት አወቃቀር፣ የብሔር፣ የመሬትና የሀብት ባለቤትነት ሲነሳ፣ ለከፍተኛ ችግር የተጋለጡት፣ ከብሔር ክልላቸው ውጭ የሚኖሩ ዜጎች ናቸው። የፌደራሉ መንግሥት፣ ለብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ ራስን በራስ የማስተዳደር እና የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት የሰጠ ቢሆንም፣ አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ግን ይህንን መብት የተመለከቱት፣ በራሣቸው ክልል በሚገኝ መሬትና ሀብት ፍጹም የባለቤትነት መብት የተሰጣቸውና የሌላው ብሔር አባል መብት እንደሌለው አድርገው ነው የሚቆጥሩት። ይህ ብቻ ሳይሆን በመንግሥት የአስተዳደር መዋቅሮች ከመወከልና ከመሳተፍ፤ ከመምረጥና መመረጥ መብት የተገለሉ ዜጎች እንደነበሩና አሁንም እንዳሉ ዶ/ር አሰፋ ይገልጻሉ።

ከ1984 ዓ.ም. ጀምሮ እንደታየው፣ በአንዳንድ ክልሎች የሌላ ብሔርና ክልል አባል የሆኑ ዜጎችን "መሬታችንንና ሀብታችንን መልሱልን፣ ከክልላችን ውጡልን" የሚሉ ጥያቄዎችና ድርጊቶች፣ ደም ላፈሰሰ፣ ሕይወት ለቀጠፈና ንብረት ላወደመ የብሔር ግጭት ምክንያት ሆነዋል። ይህ የሆነበት ዋና ምክንያት፣ የሕገ መንግሥቱን መርሆዎች፣ የፌደራል ሥርዓቱን ዓላማና መንፈስ በትክክል ካለመረዳትና የፌደራሉ መንግሥትም በክልሎች አወቃቀር ሂደት ተገቢውን ቁጥጥር አለማድረጉ ነው። የችግሩ እስከ አሁን ድረስ አለመቀረፍና የብዙዎች ሥጋት መሆኑ ደግሞ መንግሥት ትኩረት ላለመስጠቱ ዋና ማስረጃ ነው።

## መፍትሔዎቹ

በብሔር ግጭት ዙሪያ የተደረጉ አብዛኛዎቹ ጥናቶች እና የመስኩ ምሁራን፣ ግጭቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሱና አድማሳቸውን እያሰፉ መሆኑን ይናገራሉ። ለዚህም ነው ሕገ መንግሥቱንና የፌደራል ሥርዓቱን፣ ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የማስማማትና የማጣጣም ሥራ በፍጥነት ካልተደረገ የሀገሪቱ ኅልውና አደጋ ላይ ይወድቃልም ይላሉ። እንደ ዶ/ር አሰፋ ዕይታ የብሔር ግጭቶች አዳዲስ መልኮች እየያዙ መጡ እንጂ አልተባባሱም። በመጠን እና በሽፋን

ደረጃም ከፌደራሉ መንግሥት ቁጥጥር ስር የወጣና ለሀገሪቱ ኅልውና አደጋ የሆነ ጉዳይ አይደለም።

ፕ/ር ማርካኪስ፣ ረ/ፕሮፌሠር መድኃኔ፣ አቶ ዓሊ ሰይድ እና ዶ/ር አያሌው ገብሬ ጥናትና ምርምር ያደረጉባቸውን፣ የተለያዩ አካባቢ ብሔረሰብ (ጎሣ) ግጭቶችን መነሻና ሂደት መርምረውና መዝነው የሰነዘሯቸው የመፍትሔ ሃሣቦች፣ በአብዛኛው የሚያጠነጥኑት ግጭት በተደጋጋሚ በሚከሰትባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ብሔረሰቦችን (ጎሣዎችን)፣ ለዘመናት የቆዩ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ትስስሮችን ማጠናከርንና፣ ባህላዊ የግጭት መፍቻ እና ማስወገጃ መንገዶችን (traditional mechanisms of conflict resolution and prevention) ትኩረት ሰጥቶ መጠቀምን ነው። እኒህ ምሁራን በአካባቢያዊ የመንግሥት አስተዳደር መዋቅር የተፈጠሩት አርቲፊሻል ድንበሮች፣ የብሔሮችን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ትስስር እና ግንኙነት እያናጉና እያሳሱ በመሄዳቸው፣ በመንግሥት ከሚወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች ይልቅ፣ ከብሔሮች (ጎሣዎች) የሚመነጩ ባህላዊ መፍትሔዎች የላቀ ፋይዳ አላቸው ባይ ናቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ ዶ/ር አሰፋ እና ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉት የታሪክ ምሁር፣ በኢትዮጵያ ያለው የብሔር ግጭት ዘላቂ መፍትሔ ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን ካስቀመጧቸው ነጥቦች በተጨማሪ፣ ሕገ መንግሥቱንና የፌደራል ሥርዓቱን እንደገና ለመፈተሽ፣ አማራጭ ለመፈለግ እና የችግሩ መንስኤዎችና መፍትሔዎችን ለማስቀመጥ ፍቃደኝነት ይጠይቃል ይላሉ። እንደ ዶ/ር አሰፋ ሕገ መንግሥቱን እና የፌደራል ሥርዓቱን እንደገና የመፈተሹ ጉዳይ፣ የሁለቱም መርኅ እና ዓላማ ስህተት ነው ከሚል የመነጨ አይደለም። መፈተሹ የሚያስፈልገው ሕገ መንግሥቱ ለብሔር ብሔረሰቦች፣ በክልል ደረጃ የመዋቅር መብት ቢሰጥም፣ በክልል ወይም በዞን ደረጃና፣ በወረዳ ደረጃ ልንዋቀር ይገባናል በሚል ጥያቄ የሚያቀርቡ ብሔሮች ጥያቄ ግን ሲስተናገድ አይታይም። ስለሆነም ሕገ መንግሥቱ ብሔሮች (ጎሣዎች)፣ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ ደረጃ የሚዋቀሩበትን ግልጽ መርኅ ማስቀመጥ መቻል አለበት።

የፌደራል ሥርዓቱ መሠረት ያደረገው፣ የአውሮፓንና የአሜሪካን የፌደራል አወቃቀር ሥርዓት ነው። የአሜሪካ እና አብዛኛዎቹ የአውሮፓ ሀገሮች አንድና ሁለት፣ ቢበዛም ሦስት ብሔሮችን ያካተቱ ናቸው። በእነዚህ ሀገሮች የተዘረጋው የፌደራል ሥርዓት፣ ሥልጣንን ወደታችኛው የአስተዳደር ክፍል ለማውረድ (decentralization of power) ላይ ያተኮረ እንጂ፣ የብሔር ብሔረሰቦችን መብት፣ እኩልነት እና የማንነትና ራስን በራስ የማስተዳደር ዓላማ ላይ ያተኮረ አይደለም። ስለዚህም ለኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄ መፍትሔ ሊሰጥ አይችልም። በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ሊሠራ የሚችለው የፌደራል ሥርዓት የሕንድና የናይጀሪያ ሥርዓት ነው። የነዚህ ሀገሮች የፌደራል ሥርዓት፣ ሥልጣንን ወደ ክልሎች ከማከፋፈል አኳያና የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች የማንነታቸው፣ መብታቸውና እኩልነታቸው

እንዳለ ሆኖ በሀገሪቱ ሀብትና ፖለቲካ ሁሉም እኩል ባለድርሻ የሚሆኑበትን መንገድ ያመቻቸ ነው።

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሥርዓት፣ አንድ ብሔር፣ አንድ ክልል የሚለውን መስመር በመተው፣ አንድን ብሔር እንደ አመችነቱ በሁለትና ሦስት ክልል የማዋቀሩን አማራጭም ሊጠቀም እንደሚገባ ምሁራን ያመለክታሉ። አንድ ብሔር፣ አንድ ክልል የሚለው አቋምና አሠራር፣ እንደ ኦሮሚያ አማራና ሶማሌ ባሉ ክልሎች ከቆዳ ስፋት አኳያ የአስተዳደር ችግር ከመፍጠሩ ባሻገር፣ በፌደራል መንግሥት ደረጃ በሚደረጉ ውክልናዎችም በቁጥርና በቦታ አናሣ የሆኑ ብሔሮችን መብት በተወሰነ መልኩ እየተጋፋ ነው። ከዚህ በመነሣት አንድ ብሔር፣ አንድ ክልል የሚለው አቋምና አመለካከት እንደገና ሊመረመር ይገባል። በክልሎች እና በብሔሮች መሀከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በሕገመንግሥቱ መሠረት፣ አጣርቶ ውሣኔ የመስጠት ኃላፊነት የተሰጠው የፌደሬሽን ምክር ቤት ነው። ምክር ቤቱ ኃላፊነቱን በብቃትና በተገቢው ሁኔታ እየተወጣ እንዳልሆነ የተለያዩ ወገኖች ይስማሙበታል። ይህን መነሻ በማድረግም የም/ቤቱ አቅምና እንቅስቃሴ መጠናከር እንዳለበት፣ አለበለዚያም የም/ቤቱን ኃላፊነት የሚረከብ ወይም ሥራውን የሚያግዝ አካል፣ ከገለልተኛ ወገኖች መቋቋም፣ የብሔር ግጭቶችን በመፍታት ረገድ ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው ግልጽ ነው።

የታሪክ ምሁሩ ሕገ መንግሥቱንና የፌደራል ሥርዓቱን መፈተሸና ማስተካከል አስፈላጊ መሆኑን የሚስማሙበት እንደሆነ ይገልፃሉ። ከዚህ በተጨማሪ ግን መንግሥት በሚያደርጋቸው የተለያዩ ተግባሮች፣ ብሔረሰቦችን ልዩነታቸው ላይ ብቻ ማተኮሩን መተው በኢትዮጵያኖች አንድነት እንዲተኮር ማድረግ የአንድ የመፍትሔ እርምጃ ነው ይላሉ። ዘላቂው መፍትሔ ግን ሕገ መንግሥቱንና የፌደራል ሥርዓቱን እየተከሰቱ ካሉት ችግሮች አኳያ ለመፈተሽ ዝግጁ መሆን ነው። ይህ ዝግጁነት እና ፈቃደኝነት ደግሞ ሊመጣ የሚገባው ከራሱ ከሕግ አውጪው መንግሥት ነው።